# የስርአተ-ፃታ እኩልነት የገባው ትውልድ ይፈጠር

ወርቅነሽ ደምሰው

የሀገር ሰላም፣ ዴሞክራሲያዊና ፈጣን ልማት በማረጋገጥ ረገድ የሴቶች ተሳትፎ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ያለሴቶች ተሳትፎ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካው መስክ ለውጥ ለማምጣት ማሰብ በአንድ እጅ እንደማጨበጨብ ይቆጠራል፡፡ ሴቶች ምንም እንኳን የህብረተሰቡን ግማሽ ቁጥር እንደሚይዙ ቢታመንም እስካሁን በነበረው የተዛባ አመለካከት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካው መስክ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከወንዶች ጋር ሲነጻፀር ወደ ኋላ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል፡፡

ባለፉት ጊዜያት ሴቶች በተለያዩ ስራዎች ከወንዶች እኩል ተሳትፎ እንዳይኖራቸው፣ እንዳይማሩ፣ በአደባባይ ወጥተው የመናገርም ሆነ የመስራት መብታቸው ተጥሶ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው እንዲሁም በአመራር ሰጪነት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚናና ተሳትፎ ተነፍገው በማህበረሰቡ እድገት ውስጥ ምንም አይነት አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ አይችሉም በሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ ቦታ ሳይሰጣቸው ቆይቷል፡፡ ይህ አመለካከት በመቅረፍና የሴቶችን የመብት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በተለያዩ ዘርፎች በፆታ መካከል የሚታዩ የመብት ልዩነቶችን ለማስቀረት የሚያግዙ ብሔራዊ መዋቅሮች ለማጠናከር በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

እንደአገራችን ሴቶች ከወንዶች ጋር በጋብቻ፣ በስራ ቅጥር፣ በአመራርነትና በሁሉም መስኮች እኩል መብት እንዳላቸው ከዚህ በተጨማሪም ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና ለሌላ የማስተላለፍ በተለይ መሬት የመያዝና የተያያዘ የውርስ መብት እንዲሁም ቤተሰብ የማቀድና የትምህርት መብት እንዳላቸው በህገመንግሥቱ ተረጋግጧል፡፡

ኢትዮጵያ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 35 የተደነገገውን ጨምሮ የተለያዩ አለም አቀፍ የትብብር ስምምነቶች የፈረመች ሲሆን የወንጀል ህጉንም ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በህገመንግሥቱ እውቅና ከተሰጣቸው መብቶች አንጻር እንዲጣጣም በማድረግ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቤት ውስጥ ጥቃትን፣ እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ያለዕድሜ ጋብቻን፣ ጠለፋን፣ የሴት ልጅ ግርዛትን በወንጀልነት ይፈርጃቸዋል፡፡

ስለሴቶች መብትና ተጠቃሚነት በህግ፣ በፖሊሲና በስትራቴጂ በመቅረጽ እንዲሁም ከዚህ በፊት የነበረውን የተዛባ ፀረዴሞክራሲያዊ የመብት ጥሰት ከመቅረፍ፣ የሴቶች የትምህርት ደረጃ ከማሳደግና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በዚህ ረገድ ሴቶች በመሬት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኙ፤ በብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ምቹ በማድረግ ከወንዶች እኩል ተጠቃሚነት እንዲሆኑ ፤ በመኖሪያ ቤት አቅርቦት 30 በመቶ ለሴቶች ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የከተማ ልማት ፓኬጅ በመቅረጽ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ሴቶችን በማደራጀት የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

በትምህርት መስክ ‹‹ትምህርት ለሁሉም ዜጋ›› በሚለው የሚሊኒየሙ ግብ በየአቅራቢያው ት/ቤቶችን በመገንባት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ፤ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ለሚገቡ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ በማድረግ የመግቢያ ነጥብ ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ዝቅ እንዲል መደረጉ እንዲሁም ማጠናከሪያ ትምህርት ለሴቶች በመስጠት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ድጋፍ እና እገዛ እየተደረገ ነው፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ለዚህም ከምክርቤት አባል እስከ ከፍተኛ የህግ መዋቅር ድረስ የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ተሳትፎ መጨመሩ በየምርጫ ሂደቱ የሚታዩ ለውጦች ምስክር ይሆናሉ፡፡

የሴቶች የጤናና ሥነ ተዋልዶ አገልግሎትም ከቅድመ ወሊድ እስከ ድህረ ወሊድ አገልግሎት ድረስ በአቅራቢያ በሚገኝ ጤና ጣቢያዎች እየተሰጠ መሆኑ፤ የጤና አክስቴንሽን ሠራተኞች በመላው ሀገሪቱ እስከ ህብረተሰቡ ዘልቆ በመግባት አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነዚህ በተለያዩ ዘርፎች የተሰሩ ስራዎች በሴቶች ላይ የተጀመሩ የለውጥ መንገድ ጅማሮ በመሆናቸው ሊበረታቱ ይገባል፡፡ ይህንን አጠናክሮ በማስቀጠል የሴቶች ችግር ከሥር መሰረቱ በመናድ የሴቶች እኩልነትና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ ያልተሰሩ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ያልተቀረፈውን የሴቶች ችግር ግን በየጊዜው መነሳቱ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ጠለፋ ያለእድሜ ጋብቻ እና የመሳሰሉትን በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽፅኖ የሚያሳድሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በመሆናቸውን በማስቀመጥና ማህበረሰቡን በማስተማር መቀነስ ተችሏል፡፡ ችግሩን መግታት ያልተቻለበት ምክንያት በህጉ መሰረት አስተማሪ እርምጃ አወሳሰድ ላይ ክፍተት መኖሩና ህብረሰቡም የአመለካከት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን የሚደርሰው ጉዳት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንዲያመጣ አድርጎል፡፡

ሴቶች የማህበረሰቡ አንቀሳቃሽ ሞተር ናቸው፡፡ ሴቶች የእድገት ቀያሽ፤ የታሪክ ገንቢ ፤ የሀገሪቱ ተረካቢ የሆነ ትውልድ የሚያፈሩ ትውልድን የመቅረጽ ትልቁ ኃላፊነት የሚወሰድ መሠረቶች በመሆናቸው በአንድ አገር የኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ሁለገብ የሆነ ሚናን እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል፡፡

በሀገራችን በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በርካታ ልንሰራባቸው የሚገቡ የቤት ስራዎች እንዳሉ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙት አስገድዶ መድፈር፣ በሀይል የሚፈጸሙ የፆታ ጥቃት እየተበራከቱ የመጡ ሲሆን እንደነዚህ አይነቶቹ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት በቅርብ ዘመድም ፣ በባልንጀራ ፣ በጎረቤት ወዘተ የሚፈጸሙ በመሆናቸው ምክንያት አብዛኛው ወደ ህግ የማይሄዱና እዚያው ተደበስብሰው የሚቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህም አልፈው ለህግ ቀርበው የሚታዩት እንኳን ጥቂት የሚባሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሴቶች ላይ የሚደርሱት ጥቃቶች የተለያየ መልክ ያላቸው፤ዘርፈ ብዙ ጉዳትን ከማድረሳቸውም በላይ ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉትን ሴቶች ባለመሳተፋቸው እድገቱን ወደ ኋላ የሚጎትቱ ከመሆኑም ባሻገር ሴቶችን ለተለያዩ አካላዊ፣ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ቀውሶች የሚዳርጉ ናቸው፡፡

ይህ ጥቃት ለማስቆም የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ህብረተሰቡ "ሴት እናት፤ እህት እንዲሁም ሚስት ናት፡፡" የሚለውን ቢሂል ከስሩ በማስመር የህብረተሰቡ ግማሽ የሆኑት ሴቶች ያለእነርሱ ተሳትፎ እድገት ፤ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል በመገንዘብ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ሁሉም ተሳታፊ በማድረግ በበጎ አስተሳሰብ የታነጸ ስለ ሴቶች መብት ተቆርቋሪ ትውልድ የማፍራት ኃላፊነትን መወጣት ያስፈልጋል፡፡

ሴቶችን ወደ ኃላ በመጎተት ለማስቀረት እንቅፍት እየሆነ የሚያስቸግረውን ጥቃት በአንዴ ማስቆም ባይቻልም እንኳን የአስተሳሰብ ለውጦች በማምጣት መጠኑን መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህንንም ከቤተሰብ በመጀመር ለሴት ልጅ የሚሰጠው ትኩረት አካባቢን ብሎም ትምህርት ቤትን እንዲሁም ወደ ማህበረስቡን በየደረጃው በማሳደግ በሂደት የሚመጡ ለውጦችን ማሰብ ይቻላል፡፡ ለዚህም ከአስተዳደግ ጀምሮ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት በማስረጽ ያለውን የአስተሳሰብ አድማስ በማስፋትና በማስተማር በሴቶች ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን በመከላከል ረገድ መሰራት አለበት፡፡

በተያያዥነት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በተለይ ለሴቶች በጣም አሰከፊ ገጽታ እንዳለው ይታወቃል፡፡ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ቤተሰብ ተለይተውና አካባቢያቸውን ለቀው በአፈቀላጤ ደላላ ተታለውና የወላጆቻቸውን አንጡራ ሀብት ወይም ደግሞ ያላቸውን በመስጠት ስራ ፍለጋ ወደ ውጭ ሀገራት ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት የሚገጥማቸው የትየለሌ ችግሮች ውስጥ ሴቶች በቤት ሠራተኝነት እና በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰሩ ይገደዳሉ፡፡ በቤት ሰራተኝነት የተሰማሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት፣ ደሞዝ ክልከላ፣ የእንቅልፍ መነፈግ፣ የፓስፖርት መያዝ፣ በቤት ውስጥ መታገት እና ግድያን ጨምሮ አስከፊ ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል፡፡

እነዚህ ሴቶች በሀገራቸው ሊሰራቸው የሚገባ በርካታ የሥራ እድሎች በመፍጠር በሀገር በመስራት መለወጥ እንደሚቻሉ ማስገንዘብ ያሰፈልጋል፡፡ ለመለወጥ ደግሞ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ያለው የሥራ አመለካከትና ቁርጠኝነት ወሳኝ በመሆኑ መለወጥ ከራስ መጀመር አለበት፡፡ የሴቶችን ከጥቃት በማስቆም በትምህርት፣ በጤና እንክብካቤ፣ በስራ እድል ፈጠራ በፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች እኩል እድል በመስጠት በአገር እድገት ውስጥ ያለውን የሴቶች ሚና ማጉላት አስፈላጊ ነው፡፡፡

ከዚህም ሌላ የፖሊሲ አወጪዎችና በዘርፉ የተሰማሩ መንግሥታዊ ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ድርጅቶች ግለሰቦች ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተቀራርበው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሴቶች ጥቃት ለማምከን ሴቶችን በኢኮኖሚ በማብቃት የመዋዕለ ነዋይ ሆነ የክህሎት ድጋፍ ማድረግ በፖለቲካዊ መስክ ብቁ የሆኑ ሴቶችን ለማፍራት የራሳቸውን መብት ሆነ ግዴታ ለመወጣት የሚያስችላቸውን ብቃት እንዲያገኙ መደገፍ፤ ሴቶች በተሰማሩበት ስራ ውጤታማ እንዲሆኑ በማስቻል ወደፊት እንዲራመዱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የታዳጊውን ትውልድ በሚገባ በመቅረጽ ወደ ተፈለገበት ደረጃ መድረስ ይቻላል፡፡

ሴቶች በሀገር ልማት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያሉባቸውን ጋሬጣ በማስወገድ በህብረተሰቡ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ረገድ ጠንከረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም እንደ ጭላንጭል የፈነጠቀውን ብርሃን ለማስፋት ጥረቶች በማድረግ መታገል የሚያስፈልግ በመሆኑ ለዚህ የመፍትሔ ሀሳቦች ከማፍለቅና ከማገዝ ጀምሮ እያንዳንዱ ዜጋ ከሴቶች ጎን በመሰለፍ፤

ለሴቶች  መብቶች ለማስጠበቅ ለሴቶች እኩልነት የወንዶችን አጋርነት ማሳደግ እና ሥርዓተ ፆታን በማስረፅ የነቃ አስተሳሰብ ያለው የሴቶች ጥቃት የሚያንገበግበው ተቆርቋሪ ትውልድ ማፍራት ይገባል፡፡

የስርአተ-ፃታ እኩልነት የገባው ትውልድ ይፈጠር

ወርቅነሽ ደምሰው

የሀገር ሰላም፣ ዴሞክራሲያዊና ፈጣን ልማት በማረጋገጥ ረገድ የሴቶች ተሳትፎ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ያለሴቶች ተሳትፎ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካው መስክ ለውጥ ለማምጣት ማሰብ በአንድ እጅ እንደማጨበጨብ ይቆጠራል፡፡ ሴቶች ምንም እንኳን የህብረተሰቡን ግማሽ ቁጥር እንደሚይዙ ቢታመንም እስካሁን በነበረው የተዛባ አመለካከት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካው መስክ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከወንዶች  ጋር ሲነጻፀር ወደ ኋላ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል፡፡

ባለፉት ጊዜያት ሴቶች በተለያዩ ስራዎች ከወንዶች እኩል ተሳትፎ እንዳይኖራቸው፣ እንዳይማሩ፣ በአደባባይ ወጥተው የመናገርም ሆነ የመስራት መብታቸው ተጥሶ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው እንዲሁም በአመራር ሰጪነት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ሚናና ተሳትፎ ተነፍገው በማህበረሰቡ እድገት ውስጥ ምንም አይነት አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ አይችሉም በሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ ቦታ ሳይሰጣቸው ቆይቷል፡፡  ይህ አመለካከት  በመቅረፍና የሴቶችን የመብት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በተለያዩ ዘርፎች በፆታ መካከል የሚታዩ የመብት ልዩነቶችን ለማስቀረት የሚያግዙ ብሔራዊ መዋቅሮች ለማጠናከር በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

እንደአገራችን ሴቶች ከወንዶች ጋር በጋብቻ፣  በስራ ቅጥር፣ በአመራርነትና በሁሉም መስኮች እኩል መብት እንዳላቸው ከዚህ በተጨማሪም ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና ለሌላ የማስተላለፍ በተለይ መሬት የመያዝና የተያያዘ የውርስ መብት እንዲሁም ቤተሰብ የማቀድና የትምህርት መብት እንዳላቸው በህገመንግሥቱ ተረጋግጧል፡፡

ኢትዮጵያ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 35 የተደነገገውን ጨምሮ የተለያዩ አለም አቀፍ የትብብር ስምምነቶች የፈረመች ሲሆን የወንጀል ህጉንም ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በህገመንግሥቱ እውቅና ከተሰጣቸው መብቶች አንጻር እንዲጣጣም በማድረግ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቤት ውስጥ ጥቃትን፣ እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ያለዕድሜ ጋብቻን፣ ጠለፋን፣ የሴት ልጅ ግርዛትን በወንጀልነት ይፈርጃቸዋል፡፡

ስለሴቶች መብትና ተጠቃሚነት በህግ፣ በፖሊሲና በስትራቴጂ በመቅረጽ እንዲሁም ከዚህ በፊት የነበረውን የተዛባ ፀረዴሞክራሲያዊ የሙብት ጥሰት ከመቅረፍ፣ የሴቶች የትምህርት ደረጃ ከማሳደግና  ተጠቃሚነታቸውን  ለማረጋገጥ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በዚህ ረገድ ሴቶች በመሬት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኙ፤ በብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ምቹ በማድረግ ከወንዶች እኩል ተጠቃሚነት እንዲሆኑ ፤ በመኖሪያ ቤት አቅርቦት 30 በመቶ ለሴቶች ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የከተማ ልማት ፓኬጅ በመቅረጽ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ሴቶችን በማደራጀት የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

በትምህርት መስክ ‹‹ትምህርት ለሁሉም ዜጋ›› በሚለው የሚሊኒየሙ ግብ በየአቅራቢያው ት/ቤቶችን በመገንባት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ፤ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ለሚገቡ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ በማድረግ የመግቢያ ነጥብ ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ዝቅ እንዲል መደረጉ እንዲሁም ማጠናከሪያ ትምህርት ለሴቶች በመስጠት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ድጋፍ እና እገዛ እየተደረገ ነው፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ለዚህም ከምክርቤት አባል እስከ ከፍተኛ የህግ መዋቅር ድረስ  የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ተሳትፎ መጨመሩ በየምርጫ ሂደቱ የሚታዩ ለውጦች ምስክር ይሆናሉ፡፡

የሴቶች የጤናና ሥነ ተዋልዶ አገልግሎትም ከቅድመ ወሊድ እስከ ድህረ ወሊድ አገልግሎት ድረስ በአቅራቢያ በሚገኝ ጤና ጣቢያዎች እየተሰጠ መሆኑ፤ የጤና አክስቴንሽን ሠራተኞች በመላው ሀገሪቱ እስከ ህብረተሰቡ ዘልቆ በመግባት አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነዚህ በተለያዩ ዘርፎች የተሰሩ ስራዎች በሴቶች ላይ የተጀመሩ የለውጥ መንገድ ጀማሮ  በመሆናቸው ሊበረታቱ ይገባል፡፡ ይህንን አጠናክሮ በማስቀጠል የሴቶች ችግር ከሥር መሰረቱ በመናድ የሴቶች እኩልነትና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ ያልተሰሩ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ያልተቀረፈውን የሴቶች ችግር ግን በየጊዜው መነሳቱ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ጠለፋ ያለእድሜ ጋብቻ እና የመሳሰሉትን በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽፅኖ የሚያሳድሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በመሆናቸውን በማስቀመጥና ማህበረሰቡን በማስተማር መቀነስ ተችሏል፡፡ ችግሩን መግታት ያልተቻለበት ምክንያት በህጉ መሰረት አስተማሪ እርምጃ አወሳሰድ ላይ ክፍተት መኖሩና ህብረሰቡም የአመለካከት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን የሚደርሰው ጉዳት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንዲያመጣ አድርጎል፡፡

ሴቶች የማህበረሰቡ አንቀሳቃሽ ሞተር ናቸው፡፡ ሴቶች የእድገት ቀያሽ፤ የታሪክ ገንቢ ፤  የሀገሪቱ ተረካቢ የሆነ ትውልድ የሚያፈሩ ትውልድን የመቅረጽ ትልቁ ኃላፊነት የሚወሰድ መሠረቶች በመሆናቸው በአንድ አገር የኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ሁለገብ የሆነ ሚናን  እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል፡፡

በሀገራችን በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በርካታ ልንሰራባቸው የሚገቡ የቤት ስራዎች እንዳሉ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙት አስገድዶ መድፈር፣ በሀይል የሚፈጸሙ የፆታ ጥቃት እየተበራከቱ  የመጡ ሲሆን እንደነዚህ አይነቶቹ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት በቅርብ ዘመድም ፣ በባልንጀራ ፣ በጎረቤት ወዘተ የሚፈጸሙ በመሆናቸው ምክንያት  አብዛኛው ወደ ህግ የማይሄዱና እዚያው ተደበስብሰው የሚቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህም አልፈው ለህግ ቀርበው የሚታዩት እንኳን  ጥቂት የሚባሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሴቶች ላይ የሚደርሱት ጥቃቶች የተለያየ መልክ ያላቸው፤ዘርፈ ብዙ ጉዳትን ከማድረሳቸውም በላይ ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉትን ሴቶች ባለመሳተፋቸው እድገቱን ወደ ኋላ የሚጎትቱ ከመሆኑም ባሻገር  ሴቶችን ለተለያዩ አካላዊ፣ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ቀውሶች የሚዳርጉ ናቸው፡፡

ይህ ጥቃት ለማስቆም የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ህብረተሰቡ “ሴት እናት፤ እህት እንዲሁም ሚስት ናት፡፡” የሚለውን ቢሂል ከስሩ በማስመር የህብረተሰቡ ግማሽ የሆኑት ሴቶች  ያለእነርሱ ተሳትፎ  እድገት ፤ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል በመገንዘብ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ሁሉም ተሳታፊ  በማድረግ በበጎ አስተሳሰብ የታነጸ ስለ ሴቶች መብት ተቆርቋሪ ትውልድ የማፍራት ኃላፊነትን መወጣት ያስፈልጋል፡፡

ሴቶችን ወደ ኃላ  በመጎተት ለማስቀረት እንቅፍት እየሆነ የሚያስቸግረውን ጥቃት በአንዴ ማስቆም ባይቻልም እንኳን የአስተሳሰብ ለውጦች በማምጣት መጠኑን መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህንንም ከቤተሰብ በመጀመር ለሴት ልጅ የሚሰጠው ትኩረት አካባቢን ብሎም ትምህርት ቤትን እንዲሁም ወደ ማህበረሰቡን በየደረጃው በማሳደግ በሂደት የሚመጡ ለውጦችን ማሰብ ይቻላል፡፡ ለዚህም ከአስተዳደግ

ጀምሮ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት በማስረጽ ያለውን የአስተሳሰብ አድማስ በማስፋትና በማስተማር በሴቶች ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን በመከላከል ረገድ መሰራት አለበት፡፡

በተያያዥነት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በተለይ ለሴቶች በጣም አሰከፊ ገጽታ እንዳለው ይታወቃል፡፡ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ቤተሰብ ተለይተውና አካባቢያቸውን ለቀው በአፈቀላጤ ደላላ ተታለውና የወላጆቻቸውን አንጡራ ሀብት ወይም ደግሞ ያላቸውን በመስጠት ስራ ፍለጋ ወደ ውጭ ሀገራት ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት የሚገጥማቸው የትየለሌ ችግሮች ውስጥ ሴቶች በቤት ሠራተኝነት እና በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰሩ ይገደዳሉ፡፡ በቤት ሰራተኝነት የተሰማሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት፣ ደሞዝ ክልከላ፣ የእንቅልፍ መነፈግ፣ የፓስፖርት መያዝ፣ በቤት ውስጥ መታገት እና ግድያን ጨምሮ አስከፊ ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል፡፡

እነዚህ ሴቶች በሀገራቸው ሊሰራቸው የሚገባ በርካታ የሥራ እድሎች በመፍጠር በሀገር በመስራት መለወጥ እንደሚቻሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለመለወጥ ደግሞ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ያለው የሥራ አመለካከትና ቁርጠኝነት ወሳኝ በመሆኑ መለወጥ ከራስ መጀመር አለበት፡፡ የሴቶችን ከጥቃት በማስቆም በትምህርት፣ በጤና እንክብካቤ፣ በስራ እድል ፈጠራ በፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች እኩል እድል በመስጠት በአገር እድገት ውስጥ ያለውን የሴቶች ሚና ማጉላት አስፈላጊ ነው፡፡፡

ከዚህም ሌላ የፖሊሲ አወጪዎችና በዘርፉ የተሰማሩ መንግሥታዊ ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ድርጅቶች ግለሰቦች ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተቀራርበው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሴቶች ጥቃት ለማምከን ሴቶችን በኢኮኖሚ በማብቃት የመዋዕለ ነዋይ ሆነ የክህሎት ድጋፍ ማድረግ በፖለቲካዊ መስክ ብቁ የሆኑ ሴቶችን ለማፍራት የራሳቸውን መብት ሆነ ግዴታ ለመወጣት የሚያስችላቸውን ብቃት እንዲያገኙ መደገፍ፤ ሴቶች በተሰማሩበት ስራ ውጤታማ እንዲሆኑ በማስቻል ወደፊት እንዲራመዱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የታዳጊውን ትውልድ በሚገባ በመቅረጽ ወደ ተፈለገበት ደረጃ መድረስ ይቻላል፡፡

ሴቶች በሀገር ልማት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያሉባቸውን ጋሬጣ በማስወገድ በህብረተሰቡ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ረገድ ጠንከረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም እንደ ጭላንጭል የፈነጠቀውን ብርሃን ለማስፋት ጥረቶች በማድረግ መታገል የሚያስፈልግ በመሆኑ ለዚህ የመፍትሔ ሀሳቦች ከማፍለቅና ከማገዝ ጀምሮ እያንዳንዱ ዜጋ ከሴቶች ጎን በመሰለፍ፤ ለሴቶች መብቶች ለማስጠበቅ ለሴቶች እኩልነት የወንዶችን አጋርነት ማሳደግ እና ሥርዓተ ፆታን በማስረፅ የነቃ አስተሳሰብ ያለው የሴቶች ጥቃት የሚያንገበግበው ተቆርቋሪ ትውልድ ማፍራት ይገባል፡፡